# ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የካቲት 2002 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002

ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ እቃዎች የጉምሩክ ስነ ስርዓት እስከሚፈፀምባቸው ድረስ የሚቆዩበትን የጉምሩክ መጋዘኖች ደረጃ መወሰን በማስፈለጉ፣

ወደ መጋዘን የሚገባ እቃ የሚመዘገብበት መዝገብ ስለሚይዘው ዝርዝር መግለጫና ስለ አመዘጋገቡ ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት ስለሚገባ፣

መጋዘን ለመግባት የሚፈቀድላቸው ሰዎች እና ስለሚገቡበት ሁኔታ በግልጽ በማስቀመጥ ቁጥጥር ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

በጉምሩክ መጋዘን ለሚገቡ እቃዎች የሚከፈለው የመጋዘን ኪራይ ማስከፈያ ተመን ወጥ መሆን ስላለበት፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 (4)፣ 24(2)፣ 27(3) እና 30(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "ስለ ጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 40/2002 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፦

1) "የጉምሩክ መጋዘን" ማለት ገቢና ወጪ እቃዎች የጉምሩክ ስነ ስርዓት እስከሚጠናቀቅባቸው ድረስ የሚቆዩበት በባለሥልጣኑ ወይም ከባለስልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተቋቋመ ማናቸውም የእቃ ማከማቻ ቦታ ነው፡፡

2) “የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን” ማለት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመባቸው እቃዎች እንዲከማቹበት በባለስልጣኑ ፈቃድ የሚቋቋም የጠቅላላ ወይም የግል እቃ መጋዘን ነው፡፡

3) “የጠቅላላ እቃ የጉምሩክ መጋዘን” ማለት የተለያዩ አስመጪዎች ወይም ላኪዎች እቃ ላይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት እስከሚፈፀምበት ጊዜ ድረስ የሚቀመጡበት መጋዘን ነው፡፡

4) “የግል እቃ የጉምሩክ መጋዘን” ማለት ማንኛውም ሰው በስሙ ለሚያስመጣቸው ወይም ለሚልካቸው እቃዎች የጉምሩክ ስነ ስርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚከማቹበት መጋዘን ነው፡፡

5) “የመጋዘን ኪራይ” ማለት እቃውን በጉምሩክ መጋዘን በቆየበት ጊዜ ለማውረድ፣ ለመጫን፣ ለመደርደር፣ ለማስቀመጥ፣ ለመጠበቅ፣ ለመድን ዋስትና እና ለሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮች የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡

6) “የመድን ዋስትና ወይም ኢንሹራንስ” ማለት የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ባለቤት ለመጋዘኑና በመጋዘኑ ለሚከማቹ እቃዎች ደህንነት የገባው ጠቅላላ የመድን ዋስትና ነው፡፡

7) “ደንብ” ማለት የጉምሩክ መጋዘን ሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 24/1990 ነው፡፡

8) “አዋጅ” ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

9) “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በጉምሩክ መጋዘን፣ ወደ መጋዘኑ በሚገቡ እቃዎች፣ ሰዎች፣ በእቃው አስመጪ ወይም ላኪ እና በመጋዘኑ ኃላፊ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጉምሩክ መጋዘኖች ደረጃ

## 4. መሠረቱ

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (5) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መነሻ በማድረግ የጉምሩክ መጋዘኖችን ደረጃ ይወስናል፡፡

## 5. መስፈርቶች

1) ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገቡ እቃዎች በኮንቴይነር የታሸጉ እንደሆነ መጋዘኑ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን ይገባዋል፡፡

   ሀ/ ከ30 ቶን በላይ የመጫን ጉልበት ያለው መሳሪያ/ጋንትሪ/፣

   ለ/ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከ5-10 ቶን ክብደት ያለው እቃ የመጫን ጉልበት ያለው ፎርክሊፍት፣

   ሐ/ በአስፋልት ወይም በኮንክሪት የተሰራ ለእቃ ፍተሻ የሚያመች በቂ ጥላና ስፍራ ያለው የኮንቴይነር ማከማቻ ቦታ ወይም ክፍት መጋዘን፣

   መ/ ለመድሐኒት፣ ለምግብ፣ ለአደገኛና ለሌሎች እቃዎች እንደ ባህሪያቸው ለማከማቸት ወይም ለማቆየት የሚችል የተሟላ መሣሪያ ያለው ልዩና ዝግ መጋዘን፣

   ሠ/ የጉምሩክ ማሸጊያ /ሲል/፣ ማሰሪያና መቁረጫ መሣሪያ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለፁትን በሙሉ፡፡

2) የተሽከርካሪ መጋዘን፡-

   ሀ/ በአስፋልት ወይም በኮንክሪት የተሰራ ክፍት መጋዘን፣

   ለ/ ለተሽከርካሪ ፍተሻ አመቺ የሆነ የመፈተሻ ጉድጓድ/ሊፍት ያለው፣ የተሟላ ጥላ/ሼድ ያለው በቂ ቦታ፣

   ሐ/ የጐማ፣ የኤሌክትሪክ እና ተያያዥ የጋራዥ አገልግሎት መስጫ፣

   መ/ የተሽከርካሪ መጐተቻ መሣሪያ/ማሽን፣

   ሠ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለጹትን ያሟላ፣

3) በተሽከርካሪ ላይ እንዳለ የሚፈተሽ እቃ ማከማቻ መጋዘን

ሀ/ በአስፋልት የተሰራ እቃ የሚጭን ተሽከርካሪ ማቆሚያ በቂ ቦታ፣

ለ/ እንደ ሥራው ስፋት በአንድ ጊዜ ሁለትና ከዚያ በላይ በተሽከርካሪ ላይ የተጫኑ እቃ ለመፈተሽ አመቺ የሆነ የፍተሻ ማማ ያለው ጥላ/Shade/ የሆነ ክፍት የፍተሻ ቦታ፣

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለፁትን ያሟላ፣

4) በማናቸውም መጠቅለያ ለሚመጣ እቃ ማከማቻ መጋዘን፡-

ሀ/ ለምግብ፣ ለመድሐኒት፣ ለኬሚካል፣ ለአደገኛና ለሌሎች እቃዎች እንደ ባህሪያቸው ለማከማቸት የሚያስችል ከአራት ያላነሱ ዝግና ክፍት መጋዘኖች፣

ለ/ እንደ ሥራው ስፋት 3 ቶን እና ከዚያ በላይ ክብደት ያለው እቃ ለማንሳት የሚችሉ ፎርክሊፍቶች፣

ሐ/ በአየር ለሚጓጓዙ እቃዎች ማከማቻ መጋዘኖች በፖሌት ወይም አነስተኛ እቃ መጠቅለያ የታሸጉ እቃዎች የሚከማቹበት መደርደሪያ እንዲሁም ውድ የሆኑ እና ልዩ ጥበቃ የሚሹ እቃዎች ማከማቻ ሳጥን/መደርደሪያ (Safe Box/shelf)፣ እና

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተገለፁትን ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) - (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም መጋዘኖች የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ/ ለሚሰጠው የመጋዘን አገልግሎት በቂና ብቃት ያላቸው ሠራተኞች፣

ለ/ ለእቃዎቹ፣ ለሠራተኞችና ለሌሎች ንብረቶች ደኅንነት አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣

ሐ/ የእቃ ማንቀሳቀሻ ጋሪዎች፣ መሰላሎች፣ ሚዛኖች፣ መለኪያዎች፣

መ/ ለጉምሩክ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎችና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች፣

ሠ/ ከተፈቀዱ የጉምሩክ መጋዘኖች በተለያየ ምክንያቶች ያልወጡና የተያዙ እቃዎች የሚከማቹበት ዝግና ክፍት የውርስ መጋዘኖች፣

ረ/ ለሠራተኞች እና ለተገልጋዮች ተለይቶ የተዘጋጀ ክበብ እና በቂ መፀዳጃ ቦታ፣

ሰ/ ጀኔሬተር እና በቂ የውሃ አቅርቦት፣

ሸ/ ለሠራተኞች እና ለተገልጋዮች የተለዩ የተሸከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራ፣

ቀ/ በአግባቡ የተከለለ እና የመጋዘን ሥፍራዎች ከሌሎች አገልግሎት መስጫያዎችና ቢሮዎች ተለይቶ የታጠረ፣

በ/ በአስፋልት የተሰራ በቂ የተሸከርካሪዎች መተላለፊያ መንገድ፣

ተ/ በአውቶሚሽን የታገዘ የመጋዘን አስተዳደር 'Warehouse Management' ሥርዓት፣

## 6. ደረጃን ስለመወሰን

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ (1) — (4) የተዘረዘሩትን በሙሉ በአንድነት አሟልቶ የሚገኝ ማንኛውም በፈቃድ የተቋቋመ መጋዘን አንደኛ ደረጃ የጉምሩክ መጋዘን ይሆናል።
2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) - (4) ከተዘረዘሩት ውስጥ በሁለቱ ንዑስ አንቀጾች የተጠቀሱትን ያሟላ ማንኛውም መጋዘን ሁለተኛ ደረጃ የጉምሩክ መጋዘን ይሆናል።
3) በአንቀጽ 5 ስር ከሚገኙት ንዑስ አንቀጽ (1) - (4) የአንደኛውን ንዑስ አንቀጽ መስፈርቶች ያሟላ መጋዘን ሶስተኛ ደረጃ የጉምሩክ መጋዘን ይሆናል።
4) ዓለም አቀፍ የአየር መንገዶች፣ እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲሸጡ የተፈቀደላቸው ድርጅቶችና ሌሎች ባለስልጣኑ ፈቃድ በሚሰጣቸው መሠረት የሚቋቋሙ የግል መጋዘኖች አራተኛ ደረጃ የጉምሩክ መጋዘን ይሆናሉ።

## ክፍል ሶስት

## ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ እቃ አመዘጋገብ

### 7. መሠረቱ

ማንኛውም ገቢና ወጪ እቃ ወደ መጋዘን ሲገባ በዚህ መመሪያ በተወሰነው መሠረት ዝርዝር ሁኔታው እየተገለፀ በመዝገብ እና በኮምፒዩተር መመዝገብ አለበት፡፡

### 8. መዝገቡ ስለሚይዘው ዝርዝር

ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ እቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒዩተር ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝር የያዘ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ የመዝገብ ገጽ እና መለያ ቁጥር /Reference number/፣

ለ/ የእቃውን ባለቤትና  ወኪል ስም፣

ሐ/ ዲክላራሲዮን ቁጥር ወይም የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣

መ/ ወደ መጋዘን ገቢ የሆነው ጠቅላላ የጥቅል ብዛት እና የመጠቅለያው ዓይነት፣

ሠ/ የእቃዎቹ ስያሜ ከጥቅል ብዛታቸው ጭምር፣

ረ/ እቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን፣

ሰ/ የአስረካቢ እና የተረካቢ ስምና ፊርማ፣

### 9. በመዝገቡ ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

አግባብነት ያለው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የተመዘገበው የእቃ ዝርዝርና ምዝገባው ትክክል ስለመሆኑ በመመርመር በመዝገቡ እና በጭነት መግለጫ ግርጌ ላይ በመፈረም ያረጋግጣል፡፡

# ክፍል አራት

# ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት ስለሚፈቀድላቸው ሰዎችና ስለሚገቡበት ሁኔታ

## 10. መሠረቱ

1) በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት አይችልም፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት ይችላሉ፡-

ሀ/ የመጋዘኑ ኃላፊ እና ሠራተኞቹ፣

ለ/ በመጋዘኑ እቃ የመጫንና የማውረድ ሥራ የሚሰሩ ሠራተኞች፣

ሐ/ ከስራው ጋር አግባብነት ያለው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ፣

መ/ የእቃው ባለቤት ወይም ወኪል፣ ሾፌር እና ረዳት፣

## 11. ወደ ጉምሩክ መጋዘን ስለሚገባበት ሁኔታና ጊዜ

1) የጉምሩክ መጋዘን ኃላፊ፣ የመጋዘኑ ሠራተኞች እና የባለሥልጣኑ ሠራተኞች ባለሥልጣኑ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወደ ጉምሩክ መጋዘን መግባት ይችላሉ፡፡

2) በጉምሩክ መጋዘን እቃ ያለው ባለቤት ወይም ወኪል ወደ መጋዘኑ መግባት የሚችለው በእቃው ላይ ፍተሻ ወይም ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

# ስለ መጋዘን ኪራይ ተመን

## 12. መሠረቱ

1) በአዋጁ አንቀጽ 30(4) መሠረት ከመጋዘን ኪራይ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር እቃዎች በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፈልባቸዋል፡፡

2) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚከፈለው የመጋዘን ኪራይ እቃው በጉምሩክ መጋዘን ከገባ በኋላ በየፈርጁ ለማስቀመጥ፣ ለመደርደርና ሌሎች የአገልግሎት ወጪዎችን ለመሸፈን ይውላል።

## 13. የኪራይ ተመን

በጉምሩክ መጋዘን ውስጥ የገባ ማንኛውም እቃ በመጋዘን ውስጥ ለቆየባቸው ለእያንዳንዱ ቀናት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት የመጋዘን ኪራይ ይከፈልበታል።

1. በየብስ ተጓጉዘው ወደ መጋዘን ለሚገቡ ዕቃዎች

ሀ/ በዝግና እና ክፍት መጋዘን ለሚራገፉ፡-

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ/በቀናት | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1 —10 | 0.03 |
| 2 | 11 — 20 | 0.05 |
| 3 | 21 — 30 | 0.08 |
| 4 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.10 |

- ለመድን ዋስትና ሽፋን(Insurance) 0.06 ከብር 1000፣ CIF
- ለመሳሪያዎች አገልግሎት(ለመጫንና ለማውረድ) ብር 250፣ እስከ 20 ቶን
  ብር 350፣ ከ20-30 ቶን
  ብር 400፣ ከ30 ቶን በላይ

ለ/ በተሽከርካሪ ላይ እንደተጫነ ለሚፈተሹ፡-

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ/በቀናት | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1 — 10 | 0.03 |
| 2 | 11 — 20 | 0.05 |
| 3 | 21 — 30 | 0.08 |
| 4 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.10 |

- ለመድን ዋስትና ሽፋን(Insurance) 0.06 ከብር 1000፣ CIF

2. በአየር ተጓጉዞ ወደ መጋዘን ለገባ ዕቃ

| ተ.ቁ | የመጋዘን ቆይታ ጊዜ/በቀናት | ተመን/በኪሎ ግራም በብር |
|---|---|---|
| 1 | 0 — 3 | 0 |
| 2 | 4 — 10 | 0.05 |
| 3 | 11 — 20 | 0.08 |
| 4 | 21 — 30 | 0.12 |
| 5 | ከ30 ቀናት በላይ | 0.18 |

3. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ከ1 ኪሎ ግራም በታች የሚመዝን እቃ እንደ አንድ ኪሎ ግራም ተደርጐ ይወሰዳል፡፡

### *14. ከመጋዘን ኪራይ ነፃ ስለመሆን*

በአዋጁ አንቀጽ 30/4/ መሠረት በጉምሩክ መጋዘን የገባ እቃ በፍርድ ቤት ወይም በአስተዳደር የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ እቃዎቹ ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በመጋዘን ለቆየበት ጊዜ ኪራይ አይከፈልም፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### *15. የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው ግዴታ*

የጉምሩክ መጋዘን እንዲያቋቁም የተፈቀደለት ሰው በአዋጁ አንቀጽ 76 ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች መፈፀም አለበት፡፡

## *16. መመሪያውን ስለመጣስ*

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 102 መሠረት ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ተቀጥቶ ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## *17. ለሕዝብ ስለማሳወቅ*

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ ክፍል አምስት ላይ የተደነገገውን የመጋዘን ኪራይ ተመን ሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት በሕዝብ ማስታወቂያ ይገልፃል፡፡

## *18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በጉምሩክ መጋዘን የገቡ እቃዎች አፈፃፀም በነበረው መመሪያና የሕዝብ ማስታወቂያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## *19. የተሻሩ መመሪያዎች*

የጉምሩክ መጋዘኖችን ደረጃ ለመወሰን በ22/3/90 በቁጥር 02/ጉ2/26/15 የወጣው መመሪያ እና የመጋዘን ኪራይ ክፍያ መጣኔ ለመወሰን በጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ ቁጥር 1/1996 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## *20. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ*

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______________ ቀን 2002 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር